# እኛ ለኛ ሕዝባዊ መድረክ

**ቀኑ፡ እሁድ የካቲት 6፤ 2008ዓም/February 14, 2016**

**ሰዓቱ፡ 1:00 - 5:00 PM**

**ቦታ፡ Sheraton Silver Spring Hotel**
**8777 Georgia Ave,**
**Silver Spring, MD 20910**

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) **"እኛ ለኛ ሕዝባዊ መድረክ"** በሚል መሪ ሃሳብ በአገራችን መጻዒ ዕድል ላይ እሁድ የካቲት 6፤2008ዓም/February 14, 2016 በጠራው ውይይት ላይ እንዲገኙ ተጋብዘዋል፡፡ ዋናው የትኩረት ሃሳብ በአገራችን ላይ እየተፈጸመ ያለውን ኢፍትሃዊነት፣ ግፍ፣ እስር፣ ግድያ፣ እንዲሁም የአየር መዛባትና አስተዳደራዊ ብልሹነትን ተከትሎ የተከሰተው ችጋር፤ በሌላ በኩል ደግሞ እየጨመረ የመጣውን ሕዝባዊ ዓመጽ ወዴት አቅጣጫ ሊወስደን ይችላል? የሚል ሲሆን ከዚህ አንጻር በሚቀጥሉት ሳምንታት፣ ወራት፣ … የሚከሰተው ነገር የኢትዮጵያን የወደፊት ዕድል የሚወስን በመሆኑ አኢጋን የሚያበረክተውን የበኩሉን ድርሻ በተለመከተ ይሆናል፡፡

ይህ ሕዝባዊ መድረክ **"ከዘር ይልቅ ለሰብዓዊነት ቅድሚያ"** የሚሰጥባትን እንዲሁም **"ሁሉም ነጻ ሳይወጣ ማንም ብቻውን ነጻ መውጣት"** ስለማይችል ሁሉም ዜጎች በእኩልነት እና በሰብዓዊነት የሚኖሩባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመመሥረት የሚያስችል የሃሳብ ንድፍ በአኢጋን በኩል የሚቀርብበት ይሆናል፡፡

ለዚህ አዲስ የአስተሳሰብ አድማስ በጥንቃቄ ማሰብና መዘጋጀት ያስፈልገናል፡፡ ምክንያቱም አሁን ህወሃት/ኢህአዴግ በሚከተለው ዓይነት ግፈኛ የዘር/የጎሣ መቀጠል አንችልም፤ በሌላ መልኩ ደግሞ የጎሣ ፖለቲካን ቀዳሚ ያላደረገ ሌላ ዓይነት ግፈኛ የአገዛዝ ስልት ሥር መውደቅም የለብንም፡፡ አገራችን በእርስ በርስ ግጭት ወደ ውድመትና ዕልቂት እንድታመራ ፈጽሞ መፍቀድም የለብንም፡፡ **ስለዚህ ወቅቱ ስለሌሎች የምናወራበት ሳይሆን እርስበርስ የምንነጋገርበት ነው፡፡ ለመተማመን መወያየትና መነጋገር የግድ ይላል!**

በዚህ መድረክ የጋራ ንቅናቄው አገራችንን ከአስከፊ ቀውስ ለመታደግ የሚያስችል መነሻ ዕቅዱን ያቀርባል፡፡ በቀዳሚነት እርስበርሳችን ገንቢ ውይይት በማድረግ ሃሳቡን በቀጣይነት ወደ ሌሎች ባለጉዳዮች በመውሰድ የምናጋራበት ይሆናል፡፡

በዚህ ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ልጆች በሚገኙበት መድረክ እርስዎም ተገኝተው ለሰብዓዊነት ቅድሚያ ተሰጥቶባት ፍትሕ፣ ዕርቅ፣ ሰላምና ብልጽግና ሊሰፍንባት ስለሚገባት አገራችን መጻዒ ዕድል ሃሳብዎን እንዲያካፍሉ ተጋብዘዋል፡፡

**የእኛ ለሆነ ችግር የመፍትሔ ባለቤቶች እኛው ነን!**

ለተጨማሪ መረጃ አቶ ኦባንግ ሜቶን ያነጋግሩ፡ **ስልክ፡** (202) 725-1616
**ኢሜይል፡** obang@solidaritymovement.org
www.solidaritymovement.org